6ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

## 1. ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 12**

- የዜጐች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ይገነዘባሉ።
- የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይረዳሉ።
- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ዋና ዋና ተግባራትና የሥልጣን አካላት አወቃቀር ይገነዘባሉ።
- በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ያውቃሉ።
- የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መሠረቶችን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| • ዴሞክራሲ ሥርዓት ምንነትን ያብራራሉ፣<br>• በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣<br>• የሃሳብ ልዩነቶችን ምንነት ያብራራሉ፣<br>• የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖር ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• የሐሳብ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በቡድን ሥራዎችና በክበቦች በጋራ ይሳተፋሉ፣ | 1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት ትርጉም<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነት( በኢትዮጵያ ላይ ያተኮረ)<br>- የዜጐችን መብትና ጥቅሞችን በሕጋዊ መንገድ ለማስከበር፣<br>1.1.2 የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫዎች፣<br>- የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበል፣<br>-የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር፣<br>- የሕዝብ ተሳትፎ መኖር<br>- የሕዝቦች እኩልነት መከበር<br>- የመቻቻል ባሕል መኖር | • ተማሪዎች በአምስተኛ ክፍል ለዴሞክራሲ የተሰጠውን ትርጉም እንዲያስታውሱ ማበረታታት። በማስከተልም በአምተኛ ክፍል ከተማሩት ትንሽ ጠለቅ ባለ ሁኔታ ስለዴሞክራሲ ሥርዓት ትርጉም እንዲያገኙ ማድረግ።<br>• በክፍላቸው ውስጥ የተለያዩ ፍላጐቶች ያላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሰላም ለመከታተል እንዲችሉ የክፍሉ ሥርዓት ምን መልክ ሊይዝ እንደሚገባው ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• ሁሉም ተማሪዎች በሰላም እንዲማሩ ለምሳሌ አድሎ የሌለበት አሠራር ሊኖር ይገባል። ውይይታቸው በሀገር ደረጃ ከፍ ቢል ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር እንደመሆኗ መጠን የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነት የሚመነጨው የዴሞክራሲ ሥርዓት በዜጐች መካከል አድሎ እንዳይኖርና ሁሉም በእኩል መንፈስ እንዲተዳደር ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ነው ወደሚል መደምደሚያ ሊያደርሳቸው ይገባል። |
| • የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይዘረዝራሉ፣ | 1.2 የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ **(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.2.1 የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድነትና ልዩነት<br>1.2.2 የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት፣ | • ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን ስለሰብዓዊ መብቶች ሌላኛው ቡድን ደግሞ ስለዴሞክራሲያዊ መብቶች በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት በተዘረዘረው መልኩ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• ተማሪዎች ስለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ቀደም ሲል በተሰጠው ትምህርት አውቀዋል። ስለዚህ አሁን የዴሞክራሲ ሥርዓት ተግባራዊ እየሆነ ነው ለማለት ምን ምን መገለጫዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡና ትምህርቱ በአጠቃላይ ውይይት እንዲዳብር ማድረግ። ለምሳሌ በክፍል ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሠራር አለ ለማለት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ሳይሸማቀቁ በነፃነት ሊገልፁ፤ በዚህም ሒደት ቢሳሳቱም ሆነ ትክክል ቢሆኑ እንዲሸማቀቁ ያለመደረግ |

| | | |
|---|---|---|
| | | መብት አላቸው። <br> • ከዚሁ ትምህርት በመነሳትም ተማሪዎቹ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆኑ ተወያይተው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • በኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን ይዘረዝራሉ፣ <br> • አንዱ የሌላውን ማንነትና ባህላዊ መለያዎቹን (ቋንቋ ሃይማኖት፣ ወዘተ) በማክበር በቡድን ሥራዎችና በክበባት በጋራ ይሳተፋሉ፣ | 1.3 በኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከልየሚታዩ ልዩነቶች **(3 ክፍለ ጊዜ)** <br> - የቋንቋ፣ <br> -የሃይማኖት፡ <br> -የሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች፣ | • በክፍል ውስጥ በብሔር፣ ብሔረሰብ፤ በሃይማኖት ወዘተ የተለያዩ ተማሪዎች ስለአሉ ክፍሉ የሰላምና ጥሩ የመማሪያ መድረክ ይሆን ዘንድ እያንዳንዱ ተማሪ እነዚህ ልዩነቶች እንዳሉ አምኖ በመቀበል ከሌላው ተማሪ ጋር ተቻችሎና ተከባብሮ መማር ይጠበቅበታል። ይህ መቻቻል ከሌለ ግን ክፍሉ የሰላም ክፍል ሊሆን አይችልም። ተማሪዎቹ በዚህ ጉዳይ እንዲወያዩ በማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ ልዩነቶች ያሉና ወደፊት የሚኖሩ እንደሆኑ፤ በማስከተልም እነዚህን ልዩነቶች አቻችሎ መኖር ያለውን ጠቀሜታ፣ ይህ ካልሆነ ግን የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |
| • የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት የተመሠረተባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣ | 1.4 የውጪ ግንኙነት፣ **(3 ክፍለ ጊዜ)** <br> 1.4.1 ኢትዮጵያ ከጐረቤት ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት (በመልካም ጉርብትና ላይ የተመሠረተ መሆኑ)፣ <br> 1.4.2 የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረቶች | • ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሕገመንግሥት ውስጥ ስለውጪ ግንኙነት አንዱን መርህ ለተማሪዎቹ ማንበብ። ለምሳሌ አንዱ መርህ «ከጐረቤት ሀገራትና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት ጋር በየጊዜ እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ህብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጐልበት» የሚል ነው። ይህችን ሀሳብ ብቻ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ ማድረግና የኢትዮጵያን የውጪ ግንኙነት ትክክለኛነት እንዲገነዘቡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዲሞክራሲ ሥርዓት ምንነትን ያብራራሉ፣በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይዘረዝራሉ፣የሃሳብ ልዩነቶችን ምንነት ያብራራሉ፣የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖር ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የሐሳብ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በቡድን ሥራዎችና በክበቦች በጋራ ይሳተፋሉ፣በኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን ይዘረዝራሉ፣አንዱ የሌላውን ማንነትና ባህላዊ መለያዎቹን (ቋንቋ ሃይማኖት፣ ወዘተ)በማክበር በቡድን ሥራዎችና በክበባት በጋራ ይሳተፋሉ፣የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት የተመሠረተባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የዲሞክራሲ ሥርዓት ምንነትን ያብራራሉ፣በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነትን ይገልፃሉ፣የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ይዘረዝራሉ፣የሃሳብ ልዩነቶችን ምንነት ያብራራሉ፣የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖር ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የሐሳብ ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በቡድን ሥራዎችና በክበቦች በጋራ ይሳተፋሉ፣በኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን ይዘረዝራሉ፣አንዱ የሌላውን ማንነትና ባህላዊ መለያዎቹን (ቋንቋ ሃይማኖት፣ ወዘተ)በማክበር በቡድን ሥራዎችና በክበባት በጋራ ይሳተፋሉ፣የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት የተመሠረተባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ**  የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**2. የሕግ የበላይነት**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የሕገ መንግሥት አስፈላጊነትን ያውቃሉ።
- ሕግን ማክበርና ማስከበር ለዜጐች የሚኖረውን ጠቀሜታ ይረዳሉ።
- የሕዝብ ተመራጮችና የመንግሥት ባለሥልጣናት የሥልጣን ገደብ የሚጣልባቸው መሆኑን ይረዳሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • የክልል ሕገመንግሥቶ ችን አስፈላጊነት ያብራራሉ፣<br>• የአካባቢ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይገነዘባሉ፣<br>• ሁሉም ዜጋ ሕግን የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በምሳሌ ያስረዳሉ፣ | 2.1 ሕገመንግሥት ምንድን ነው? (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>(መጠነኛ ክለሳ)<br>2.1.1 የክልል ሕገመንግሥታት አስፈላጊነት፡<br>2.1.2 የአካባቢ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስከበር ረገድ ያላቸው ድርሻ፣<br>2.1.3 ሕግን አለማስከበር በዜጐች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት፣ | • በ5ተኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርታቸው ስለ ሕገመንግሥት እንዲያውቁ ተደርጓል። በዚህ ትምህርት ላይ ደግሞ ሕገመንግሥት ምንድን እንደሆነ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲገልፅ በማድረግ ስለ ሕገመንግሥት ምንነት ክለሳ እንዲካሄድ ማድረግ።<br>• በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥቶችን እንዲያነቧቸው በማድረግ አንድነትና ልዩነቶቻቸውን እንዲገልፁ ማድረግ። ከዚህም በመነሳት የክልል ሕገመንግሥት አስፈላጊነትን በቡድናቸው ውስጥ ተወያይተው በአጠቃላይ የክፍል ውይይት እንዲያዳብሯቸውና የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ።<br>• በሌላ በኩል እነሱ የሚያውቋቸውን የአካባቢ ባህላዊ ደንቦችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። የማያውቁ ከሆነ ቤተሰቦቻቸውን ወይም የሚያውቅ ሰው በመጠየቅ እንዲያስረዱና እነዚህ ደንቦች ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• ሕግን ማክበርና ማስከበር ለዜጐች የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲሁ እንዲወያዩበትና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሥነምግባር ምንነትን ይገልፃሉ፣<br>• በትምህርት ቤት ደረጃ ከነሱ የሚጠበቁ ሥነምግባሮችን ይዘረዝራሉ፣ | 2.2 ሥነምግባር (**2 ክፍለ ጊዜ**)<br>2.2.1 የሥነምግባር ምንነት (አጭር መግለጫ)<br>2.2.2 በትምህርት ቤት ደረጃ የሚጠበቅ የተማሪ | • ሥነምግባርን ባጭሩ መግለጽ። ለምሳሌ ሥነምግባር አንድን ባህሪ፣ ተግባር ወዘተ ጥሩ ወይም መጥፎ በማለት የምንለይበት የሞራል መለኪያ ነው። ይህን ጉዳይ ተማሪዎቹ እንዲጨብጡ ከተደረጉ በኋላ እንደተማሪነታቸው በትምህርት ቤት ደረጃ ከነሱ የሚጠበቁ የተማሪ ሥነምግባሮች ምን እንደሆኑ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ለምሳሌ በትምህርት ቤት ደረጃ መምህራኖቻቸው ንና የጊቢውን ማህበረሰብ ባጠቃላይ ማክበር፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት ከጥፋት መከላከልና የጊቢውን |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | ሥነምግባር፣<br>- የትምህርት ቤቱንና የክፍሉን ደንቦች ማክበርና ማስከበር፣<br>- የትምህርት ቤቱንና የክፍሉን ንብረቶች ከጉዳት መከላከል፣<br>- የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማክበር፣<br>- የትምህርት ቤቱንና የመማሪያ ክፍልን ጽዳትና ውበት መጠበቅ፣ | ውበት መጠበቅ ወዘተ ሊግባቡባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። |
| • የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ መጣል ለምን እንዳስፈለገ ያስረዳሉ፣ | 2.3 የሥልጣን ገደብ፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.3.1 የሥልጣን ገደብ ምንድን ?<br>2.3.2 በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ የመጣል አስፈላጊነት፣ | • በመጀመሪያ አንድ ነገር ላይ ገደብ መጣል ለምን እንደሚያስፈልግ ባጭሩ መግለጽ። ለምሳሌ እግር ኳስ የሚጫወቱበት ሜዳ በስፋቱና በርዝመቱ የተወሰነ ነው። ከዚያ ወጥቶ መጫወት ከመጣ ጨዋታው ይበላሻል።<br>• እንደዚሁም የክፍል አለቃቸው ያለው ሥልጣን የተገደበ ነው። የክፍል ፀጥታ የሚያውኩ ተማሪዎችን ለክፍል ኃላፊ መምህር በማቅረብ ተፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል። ከዚህ አልፎ ግን ተማሪዎችን የሚደበድብ ወይም ክፍል እንዳይገቡ የሚከለክል ከሆነ የትምህርት ቤት ሥርዓት ይበላሻል። እንዲህ እያለ ከክፍል አለቃ እስከ ሀገር መሪ<br>• የሥልጣን ገደብ አለበት። ተማሪዎቹ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ በማድረግ በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ የመጣልን አስፈላጊነት ላይና ይህ ባይሆን ሊከተል የሚችለውን ችግር እንዲወያዩ በማድረግ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |
| • የጓደኛን ሚስጥር ማባከን የሚያስከትለውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ | 2.4 ሚስጥር፣ (1 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.4.1 የጓደኛ ሚስጥር፣<br>- የጓደኛን ሚስጥር አለማባከን፣ | • ሚስጥር በጥንቃቄ ሊያዝ የሚገባና ለማንም ሊነገር የማይገባ ጉዳይ መሆኑን እንዲከልሱ ማድረግ። በመሆኑም ሚስጥር መባከን የማይገባውና ከባከነ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ ለምሳሌ ጓደኞችን የነገረንን ሚስጥር ብናባክን በመካከላችን ምን ሊከሰት እንደሚችል ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው |

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| | -የጓደኛን ሚስጥር ማባከን የሚያስከትለው ጉዳት፣ | እንዲወያዩ ማድረግ። ይህን ውይይት በክፍል ተጨማሪ ውይይት ማጠናከርና ተማሪዎች በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ኃላፊነታቸውን በዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣ | 2.5 ሙስና፡ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>2.5.1 የሙስና ምንነት (ከአምስተኛ ክፍል የተለየ ግን አጭር መግለጫ)<br>2.5.2 ኃላፊነታቸውን በዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራት፣ | • ተማሪዎቹ በመጀመሪያ የሕዝብ ተማራጮችና የመንግሥት ባለሥልጣናትን ልዩነት እንዲገልጹ ማድረግ። እነዚህ ወገኖች በሕዝብና በመንግሥት አመኔታ አግኝተው ሥልጣን የተሰጣቸው መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ።<br>• በማስከተልም ሙስና ምን እንደሆነ በ5ኛ ክፍል የተማሩትን በማስታወስ እንዲያብራሩ ማድረግ። የሕዝብ ተመራጮችና የመንግሥስት ባለሥልጣናት ያላቸውን ሥልጣን በመጠቀም የተለያዩ የሙስና ተግባራትን ሊፈጽሙ እንደሚችሉ እንዲወያዩና በራሳቸው መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

- **ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የክልል ሕገመንግሥቶ ችን አስፈላጊነት ያብራራሉ፣የአካባቢ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይገነዘባሉ፣ሁሉም ዜጋ ሕግን የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በምሳሌ ያስረዳሉ፣የሥነምግባር ምንነትን ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤት ደረጃ ከነሱ የሚጠበቁ ሥነምግባሮችን ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ መጣል ለምን እንዳስፈለገ ያስረዳሉ፣የጓደኛን ሚስጥር ማባከን የሚያስከትለውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ኃላፊነታቸውን በዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣
- **ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የክልል ሕገመንግሥቶ ችን አስፈላጊነት ያብራራሉ፣የአካባቢ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስፈን ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይገነዘባሉ፣ሁሉም ዜጋ ሕግን የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በምሳሌ ያስረዳሉ፣የሥነምግባር ምንነትን ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤት ደረጃ ከነሱ የሚጠበቁ

ሥነምግባሮችን  ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ መጣል ለምን እንዳስፈለገ ያስረዳሉ፣የኋደኛን ሚስጥር ማባከን የሚያስከትለውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ኃላፊነታቸውን በዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣

- **ውጤታቸው ዝቅተኛ**  የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 3. እኩልነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የኢትዮጵያ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ይገነዘባሉ።
- ሴቶች በልማትና በሀገር ግንባታ ሊኖራቸው የሚገቡ ተሳትፎዎችንም ያውቃሉ።
- የአካል ጉዳተኞች በትምህርት ቤት ደረጃ ሊኖራቸው የሚገቡ መብቶችን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን መብቶችን ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ያከብራሉ፣ | 3.1 የእኩልነት መብቶች፣(3 ክፍለ ጊዜ)<br>3.1.1 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች፣<br>3.1.2 በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች የሚጠቀሙባቸው ተቋማት፣<br>- ተቋማቱ የማህበረሰቡን እኩል ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡባቸው መንገዶች፣<br>3.1.3 የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ማክበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ፣ | • የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብቶች በፌዴራል ሕገመንግሥቱ በማያሻማ መልኩ ሰፍሯል። ተማሪዎቹ ይህንን እንዲረዱ ከፌዴራል ሕገመንግሥቱ በተለይ አንቀጽ 39ን፣ 40ን፣ 41ን፣ እንዲያነቧቸው ማድረግ። በማስከተ ልም የሁሉም መብት መከበሩ ምን ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የቡድን ውይይቱን በክፍል የጋራ ውይይት በማጠናከር በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መርሆን በተመለከተ ተማሪዎች ሰፊና ተጨባጭ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ በፕሮጀክት መልክ የአካባቢያቸውን ሁኔታ እንዲያጠኑ ማድረግ። |

6ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የብሔሮች ብሔረሰቦ ችና ሕዝቦች ባህሎች እኩል እንዲከበሩ ሊደ ረጉ የሚገቡ ተግባራ ትን ይዘረዝራሉ፣<br>• በልማትና በሀገር ግንባታ የሴቶች እኩል ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው የሴት ተማሪዎችን እኩልነት ያከብራሉ፣ | 3.2 የእኩልነት መገለጫዎች፣<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.2.1 የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መገለጫዎች ፣<br>- የቋንቋዎች እኩልነት<br>- የፆታ እኩልነት<br>3.2.2 የሴቶች እኩል ተሳትፎ ለልማትና ለሀገር እድገት፣<br>- ለሀገር ግንባታ የሴቶች እኩል ተሳትፎ አስፈላጊነትና የሚኖረው ጠቀሜታ፣ | • ተማሪዎቹ ቀደም ባለው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን የኢ.ፌ.ዴ.ሪን ሕገመንግሥት አንቀጾች ማለትም አንቀጽ 39ን፣ 40ን፣ 41ን፣ እንዲያነቧቸው ማድረግ። ከዚህ በመነሳትም በሕገመንግሥቱ አንቀጾች መንፈስ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ መገለጫዎች እንዲከበሩ ከነሱና ከሌሎች ወገኖችም ምን እንደሚጠበቅ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግና የውይይት ውጤታቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• በክፍላቸው ውስጥ የፆታ ስብጥርን በተመለከተ ወንዶች ስንት እንደሆኑ፣ ሴቶች ስንት እንደሆኑ ቆጥረው እንዲናገሩ ማድረግ። አንድ ውሳኔ የሚሻ ነገር ለተማሪዎቹ ማቅረብና ይህን ውሳኔ ማን መወሰን እንደሚገባው ተማሪዎቹ እንዲያስረዱ ማድረግ። እንደሚታወቀው ውሳኔው መወሰን ያለበት በሁሉም ተማሪ እንጂ በወንዶች ወይም በሴቶች ብቻ መሆን አይችልም (በድምፅ ብልጫ የበለጠ ድምፅ ያገኘው ወገን ውሳኔ ተቀባይነት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው) ፣<br>• እንደዚሁም በልማትና በአጠቃላይ በሀገር ግንባታ ወንዶችና ሴቶች እኩል መብት ኖሯቸው ካልተሳተፉ የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ እንደማይችል ግልጽ ነው። በዚህ ላይ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ ማድረግና የሴቶች መብቶቻቸው ሊከበሩላቸው እንደሚገቡ ይህም የሚኖረውን ጠቀሜታ በተመለከተ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የአካል ጉዳተኞች ሊኖሯቸው የሚገቡ መብቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ያከብራሉ፣<br>• ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፣ | 3.3 የአካል ጉዳተኞች ሊኖሯቸው የሚገቡ መብቶች፣ **(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>-አካል ጉዳተኞች በትምህርት ቤት ደረጃ ሊኖሯቸው የሚገቡ መብቶች፣ | • በ5ኛ ክፍል ላይ ተማሪዎቹ ስለአካል ጉደተኝነትን የተማሩትን እንዲያስታውሱት ማድረግ። በማስከተልም ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ምን ምን መብቶች እንዳሏቸው እንዲገልጹ ማድረግ። ተማሪዎቹ አለን የሚሏቸው መብቶች ሁሉ አካል ጉዳተኞች እንዳላቸው በውይይት አማካኝነት እንዲያዳብሩት ማድረግ፣ |
| • የሃይማኖት እኩልነትን ያከብራሉ፣ | 3.4 የሃይማኖት እኩልነት መከበር አስፈላጊነት **(1ክፍለ ጊዜ)** | • ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉትን ሃይማኖቶች እንዲገልጹ ማድረግ። እንዲሁም እነሱ የምን ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ። ከዚያም ሃይማኖታቸውን አንድ ሰው ቢያንቋሽሽባቸው ምን እንደሚሰማቸው እንዲገልጹ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| | | ማድረግ። ከዚህ በመነሳት የሃይማኖት እኩልነት አስፈላጊነትን እራሳቸው ድምዳሜ እንዲሰጡበት ማድረግና ትምህርቱን ማጠናቀቅ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ይዘረዝራሉ፣የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን መብቶችን ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ያከብራሉ፣የብሔሮች ብሔረሰቦ ችና ሕዝቦች ባህሎች እኩል እንዲከበሩ ሊደ ረጉ የሚገቡ ተግባራ ትን ይዘረዝራሉ፣በልማትና በሀገር ግንባታ የሴቶች እኩል ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሴት ተማሪዎችን እኩልነት ያከብራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ይዘረዝራሉ፣የእኩልነትና እኩል ተጠቃሚነትን መብቶችን ማክበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ያከብራሉ፣የብሔሮች ብሔረሰቦ ችና ሕዝቦች ባህሎች እኩል እንዲከበሩ ሊደ ረጉ የሚገቡ ተግባራ ትን ይዘረዝራሉ፣በልማትና በሀገር ግንባታ የሴቶች እኩል ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤታቸው የሴት ተማሪዎችን እኩልነት ያከብራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 4. ፍትሐዊነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- በአካባቢያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማትን አስፈላጊነትን ይገነዘባሉ።
- የማህበራዊ ተቋማት አሰራሮች ከአድሎ የፀዱና ፍትሐዊ ሊሆኑ እንደሚገቡ ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በአካባቢያቸው የሚታዩ አድሎአዊ አሰራሮችን ይመረምራሉ፣<br>• አድሎአዊ አሠራሮች ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• በአካባቢያቸው ፍትሐዊ አሠራሮች እንዲሰፍኑ ያቅማቸውን ያህል ጥረት ያደርጋሉ፣ | 4.1 አድሎአዊ አሠራሮች፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>4.1.1 በአካባቢያችን የሚታዩ የልዩ ልዩ አድሎአዊ አሰራሮች መግለጫ ተግባራት፣ | • ለመግቢያ እንዲያገለግል አድሎአዊ አሠራር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስረዳ ማድረግ። ፍትሐዊ ወይንም አድሎአዊ አሠራሮች ምን ጊዜም ቢሆን ሊከሰቱ የሚችሉት የተግባር እንቅስቃሴ ባለበት ሁኔታ ነው። ለምሳሌ በትምህርት ቤት ወይም በቀበሌ አስተዳደር ውስጥ ሥራ አለ ስለሆነም ፍትሐዊ ወይንም አድሎአዊ አሠራሮች አሉ። ተማሪዎች ይህን ጉዳይ በውል እንዲገነዘቡ በማድረግ በአካባቢያቸው የሚከሰቱ አድሎአዊ አሠራሮችን እንዲሁም እነዚህን አድሎአዊ አሠራሮችን ለማስቀረት ምን ሊደረግ እንደሚገባው በቡድን ተከፋፍለው ውይይት እንዲያደርጉና ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ። |
| • በአካባቢያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማት የሚያሳዩትን የአሠራር ፍትሐዊነትን ይገመግማሉ፣ | 4.2 ማህበራዊ ተቋማት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>4.2.1 በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚያሳዩት የአሰራር ብቃትና ፍትሐዊነት፣ | • በመጀመሪያ በአካባቢያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል ወላጆቻቸውን ወይም የቀበሌ አስተዳደሮችን በመጠየቅ እነዚህ ተቋማት ምን ያህል ውጤታማ አገልግሎት እንደሚሰጡና ፍትሐዊነታቸውንም በክፍል ውስጥ እንዲያስረዳ ማድረግ።<br>• በአመራጭነትም በቀበሌያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማትን እንዲጎበኙና በተቋማቱ የአሠራር ብቃትና ፍትሐዊነት ላይ በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ ማድረግ። |
| • የመብት መጣስና የፍትህ መጓደል መንስዔዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 4.3 የመብት መጣስና የፍትህ መጓደል መንስዔዎች፣ | • በትምህርት ቤታቸው፣ በቤታቸው ወይም በቀበሌያቸው አድሎ ይፈፀም እንደሆነ እያንዳንዱ ተማሪ አስተያየቱን እንዲሰጥ ማድረግ፣ አድሎው እንዴት |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የጓደኞቻቸውን መብቶች ያከብራሉ፣<br>• የክፍል ጓደኞቻቸውን በእኩልነት ያስተናግዳሉ፣ | **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>-የዜጐችን መብቶች አለማክበር፣<br>-በተሰጠ ሥልጣን አላግባብ መገልገል<br>-ዜጐችን በእኩልነት መንፈስ አለማስተናገድ፣ | እንደሚገለጽ እንዲሁ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲገልጽ ማድረግ።<br>• አድሎ የሚፈፀም ከሆነ ምን እንደሚከሰት (የመብት መጣስና የፍትህ መጓደል) ተማሪዎቹ እንዲወያዩና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ለፍትህ መስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 4.4 ፍትህ እንዲኖርየሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>-ፍትሐዊ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣<br>- የአካባቢ የፍትህ አካላት በተሰጣቸው ሥልጣንና በሕግ መሠረት ብቻ መሥራት፣<br>- ዜጐች ፍትህ የማግኘት መብታቸውን መጠቀም፣<br>-መብትን ለማስከበርና ፍትህን ለማግኘት የተነሳሽነት ስሜት መኖር፣ | • በክፍላቸው፣ በትምህርት ቤታቸው፣ ወይም በቀበሌያቸው የነሱን መብት የሚጥስ አንድ ጭብጥ ለተማሪዎቹ ማቅረብ። በዚህ ጭብጥ ላይ ተነስተው መብታቸውን ለማስከበር ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በቡድን ተወያይተው የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• ዋናው ቁም ነገር ፍትህን ለማስከበር የፍትህ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ማንም ሰው ቢሆን መብቱ ሲጣስ ፍትህን ለማግኘት ማንንም ሳይጠብቅ በተነሳሽነት ስሜት መብቱን ማስከበር የሚጠበቅበት መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ማስረዳት ነው። |
| • ግብር መቼ እንደተጀመረ ይገልፃሉ፣<br>• ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣ | 4.5 ግብር፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>4.5.1 ግብር መቼና እንዴት ተጀመረ? | • በ5ኛ ክፍል ስለ ግብር ምንነት ተምረዋል። ያንን ትምህርት እንዲከልሱት ማድረግና በግብር መክፈል ላይ ስምምነት እንዲኖር ማድረግ። ግብር የሚጣልባቸውን የገቢ ዓይነቶች እንዲያውቁ ከተደረገ በኃላ፤ በግብር መክፈል |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የግብር አከፋፈልን በተመለከተ ከዜጐች ምን እንደሚጠበቅ ያስረዳሉ፣<br>• ግብርን በታማኝነት መክፈል የዜጐች ግዴታ መሆኑን ያስረዳሉ፣ | 4.5.2 ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ልዩነቶች፣<br>4.5.3 ግብርን በሀቀኝነት መክፈል የዜጐች ግዴታ መሆኑ፣ | ላይ ስምምነት ተደርሷልና ግብርን በትክክል ለመክፈል ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን እንደሚጠበቅ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና ግብርን በሀቀኝነትና ታማኝነት መክፈል የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በአካባቢያቸው የሚታዩ አድሎአዊ አሰራሮችን ይመረምራሉ፣አድሎአዊ አሠራሮች ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣ በአካባቢያቸው ፍትሐዊ አሠራሮች እንዲሰፍኑ ያቅማቸውን ያህል ጥረት ያደርጋሉ፣በአካባቢያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማት የሚያሳዩትን የአሠራር ፍትሐዊነትን ይገመግማሉ፣የመብት መጣስና የፍትህ መጓደል መንስዔዎችን ይዘረዝራሉ፣የጓደኞቻቸውን መብቶች ያከብራሉ፣ የክፍል ጓደኞቻቸውን በእኩልነት ያስተናግዳሉ፣ለፍትህ መስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣ግብር መቼ እንደተጀመረ ይገልፃሉ፣ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣የግብር አከፋፈልን በተመለከተ ከዜጐች ምን እንደሚጠበቅ ያስረዳሉ፣ግብርን በታማኝነት መክፈል የዜጐች ግዴታ መሆኑን ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** በአካባቢያቸው የሚታዩ አድሎአዊ አሰራሮችን ይመረምራሉ፣አድሎአዊ አሠራሮች ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣ በአካባቢያቸው ፍትሐዊ አሠራሮች እንዲሰፍኑ ያቅማቸውን ያህል ጥረት ያደርጋሉ፣በአካባቢያቸው የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማት የሚያሳዩትን የአሠራር ፍትሐዊነትን ይገመግማሉ፣የመብት መጣስና የፍትህ መጓደል መንስዔዎችን ይዘረዝራሉ፣የጓደኞቻቸውን መብቶች ያከብራሉ፣ የክፍል ጓደኞቻቸውን በእኩልነት ያስተናግዳሉ፣ለፍትህ መስፈን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣ግብር መቼ እንደተጀመረ ይገልፃሉ፣ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣የግብር አከፋፈልን በተመለከተ ከዜጐች ምን እንደሚጠበቅ ያስረዳሉ፣ግብርን በታማኝነት መክፈል የዜጐች ግዴታ መሆኑን ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 5. የሀገር ፍቅር

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን ይገነዘባሉ።
- የሀገርን ታሪክ ማወቅ ለሀገር ፍቅር መጎልበት ያለውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዓላማን ይረዳሉ።
- ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ለሀገር ፍቅር መኖር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ታሪክ ማወቅ ይሻሉ፣ | 5.1 የሀገር ፍቅር፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>5.1.1 ለሀገር ፍቅር መጎልበት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፣<br>- የግልና የቡድን መብቶች መከበር፣<br>- አድሎአዊ አሠራር አለመኖር፣<br>- የአካባቢንና የሀገርን ታሪክ ማወቅ፣ | • ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል የግልና የቡድን መብቶች ምን እንደሆኑ እንዲወያዩ ማድረግ። ከዚሁ ጋር ክፍላቸው ጥሩ የመማሪያ ክፍል እንዲሆንና እነሱም በክፍላቸው እንዲኮሩ ከግልና ከቡድን መብት አንፃር ክፍላቸው ምን መምሰል እንደሚገባው በቡድናቸው ተወያይተው ለአጠቃላይ ክፍሉ በየተራ እንዲያስረዱ ማድረግ።<br>• ከዚሁ ጋር ተጠናክሮ ግንዛቤ መውሰድ የሚገባው ስለ ክፍላቸውም ሆነ ስለትምህርት ቤታቸው ወይም ስለአካባቢያቸው ጥሩ ፍቅር ሊኖራቸው የሚችለው ታሪካቸውንና ማንነታቸውን ሲያውቁ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ነው። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ሚስጥር የሚባክንባቸውን መንስዔዎች ይዘረዝራሉ፣<br>• የተነገራቸውን ሚስጥር ይጠብቃሉ፣<br>• ለትምህርት ቤት ንብረቶች እንክብካቤ ያደርጋሉ፣<br>• ቆሻሻዎችን በተገቢው ቦታ አጠራቅመው ይጥላሉ፣ | 5.2 ጐጂና አፍራሽ ተግባራት፣<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>- ለጋራ ንብረቶች እንክብካቤ አለማድረግ፣<br>- በትምህርት ቤት ውስጥ ለጋራ መገልገያ ንብረቶች ተገቢውን እንክብካቤ አለማድረግ የሚያስከትለው ጉዳት፣<br>- ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣<br>-በመፀዳጃ ቤት ባግባቡ አለመጠቀም፣<br>- ግዴለሽነት፣ | • ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ሚስጥር ምን እንደሆነና ለሚስጥር መባከን መንስዔዎች ምን እንደሆኑ እንዲወያዩ ማድረግ። እንዲሁም በትምህርት ቤት የሚታዩ ጐጂ አፍራሽ ተግባራት የሚሏቸውን ዘርዝረው እንዲወያዩባቸው ማድረግ።<br>• ይህን የቡድን ውይይት ክፍል ውስጥ በጋራ እንዲነጋገሩባቸው ማድረግና የትምህርት ቤት ንብረትን ጐጂ በሆነ መልኩ መገልገል ተገቢ እንዳልሆነና በጥንቃቄ መገልገል እንደሚያስፈልግ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |
| • የበጐ ባህሪያት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠበቁባቸውን በጐ ባህሪያት ያዳብራሉ፣ | 5.3 በጐ ባህሪያት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>5.3.1 ማንኛውንም አፍራሽ ተግባር መቃወም፣<br>- ሌባን ማጋለጥ፣<br>- አድሎአዊ አሠራርን አለመቀበል፣<br>- ያልተረጋገጠን ወሬ አለመቀበል፣ | • በቀደመው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎቹ ጐጂና አፍራሽ ተግባራትን እንዲለዩ ተደርገዋል። በነኝህ ክፍላተ ጊዜያት ደግሞ እነሱ በጐ ባህሪያት የሚሏቸውን በቡድን ተወያይተው እንዲዘረዝሯቸው ማድረግና የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ። |
| • ድህነትን ለማስወገድ የፖሊሲዎችና የስትራቴጂዎች አስፈላጊነት ያብራራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በጐ | 5.4 ድህነትን ማስወገድ፣(2 ክፍለ ጊዜ)<br><br>5.4.1 ድህነትን ለማስወገድ | • በ5ኛ ክፍል ድህነትን ለማስወገድ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች እንዲያውቁ ተደርገዋል። እዚህ ጋ ትኩረቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ መሆን አለበት። እነሱ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚሰሩትን አውቀውና አቅደው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ፈቃደኝነት የሚጠይቁትን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አቅማቸው በፈቀደው በበጐ ፈቃደኝነት ተግባራት ይሳተፋሉ፣ | የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስፈላጊነት፣<br>5.4.2 በቤና በትምህርት ቤት ውስጥ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት መፈፀም | • ድህነትን ለማስወገድ እንዲሁ አቅዶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም መመሪያዎች ሲሆኑ ድህነትን ለማስወገድ ምን ላይ ማተኮር እንደሚያስፈልግ፣ ምን ምን ተግባራት መከናወን እንደሚገባቸው የሚገልጹ ናቸው። ስለሆነም ተማሪዎች ይህን እንዲረዱ በሚገባቸው መንገድ ማወያየትና ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣<br>• እራሳቸው ዜግነት ያገኙበትን መንገድ ይገልፃሉ፣<br>• የሰንደቅዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉምን ይገልፃሉ። | 5.5 ዜግነት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>5.5.1 ዜግነት የሚገኝባቸው መንገዶች፣<br>- በመውለድ የሚገኝ ዜግነት፣<br>- በሕግ የሚሰጥ ዜግነት፣<br>5.6 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ<br>5.6.1 የሰንደቅዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉም | • በ5ኛ ክፍል ላይ የዜግነት ትርጉምን እንዲያውቁ ተደርጓል። እዚህ ጋ ያን ትምህርት በመከለስ በኢትዮጵያ ውስጥ ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ማስረዳትና የበለጠ በውይይት እንዲያዳብሩት ማድረግ።<br><br>• የኢትጵያን ሰንደቅዓላማ ለማቅረብና ቀለማቱን እንዲናገሩ ማድረግ፣ ቀለማቱን ከለዩ በኋላ የቀለማቱን ትርጉም እንዲገልጹ ማድረግ፣ በማስከተልም ዓርማውን በማሳየት የዓርማውን ትርጉም በራሳቸው እንዲናገሩ ማድረግ። በመጨረሻም የሰንደቅዓላማን አስፈላጊነትና ሊሰጠው የሚገባውን ክብር አስመልክቶ ተማሪዎች በተራ እንዲናገሩ በማድረግ ትምህርቱን ማጠናቀቅ፣ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ለሀገር ፍቅር መኖር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ታሪክ ማወቅ ይሻሉ፣ሚስጥር የሚባክንባቸውን መንስዔዎች ይዘረዝራሉ፣የተነገራቸውን ሚስጥር ይጠብቃሉ፣ለትምህርት ቤት ንብረቶች እንክብካቤ ያደርጋሉ፣ቆሻሻዎችን በተገቢው ቦታ አጠራቅመው ይጥላሉ፣የበጐ ባህሪያት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠበቁባቸውን በጐ ባህሪያት ያዳብራሉ፣ድህነትን ለማስወገድ የፖሊሲዎችና የስትራቴጂዎች አስፈላጊነት ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በጐ ፈቃደኝነት የሚጠይቁትን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አቅማቸው በፈቀደው በበጐ ፈቃደኝነት ተግባራት ይሳተፋሉ፣ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣እራሳቸው ዜግነት ያገኙበትን መንገድ ይገልፃሉ፣የሰንደቅዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉምን ይገልፃሉ።

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ለሀገር ፍቅር መኖር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ታሪክ ማወቅ ይሻሉ፣ሚስጥር የሚባክንባቸውን መንስዔዎች ይዘረዝራሉ፣የተነገራቸውን ሚስጥር ይጠብቃሉ፣ለትምህርት ቤት ንብረቶች እንክብካቤ ያደርጋሉ፣ቆሻሻዎችን በተገቢው ቦታ አጠራቅመው ይጥላሉ፣የበጐ ባህሪያት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠበቁባቸውን በጐ ባህሪያት ያዳብራሉ፣ድህነትን ለማስወገድ የፖሊሲዎችና የስትራቴጂዎች አስፈላጊነት ያብራራሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በጐ ፈቃደኝነት የሚጠይቁትን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አቅማቸው በፈቀደው በበጐ ፈቃደኝነት ተግባራት ይሳተፋሉ፣ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፣እራሳቸው ዜግነት ያገኙበትን መንገድ ይገልፃሉ፣የሰንደቅዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉምን ይገልፃሉ።

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 6. የኃላፊነት ስሜት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ** 10

- የኃላፊነት ድርሻን በወቅቱ በታማኝነትና በብቃት መወጣት ዜጐች ግዴታ እንዳለባቸው ይረዳሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ከውድመት መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን ይገነዘባሉ።

| **ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች** | **ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች** | **በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት** |
|---|---|---|
| • በቤተሰብ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የቃል ኪዳን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣ | 6.1 ቃል ኪዳን፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>6.1.1 በቤተሰብ ውስጥ ሊከበሩ የሚገቡ ቃል ኪዳኖች፣<br>- ቤተሰብን ማክበር፣<br>- የቤተሰብን ምክር መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ፣<br>- ቤተሰብን በቤት ውስጥ ሥራ ማገዝ፣ | • ቃል ኪዳን በተቻለ መጠን ሊጠበቅ የሚገባ የሀሳብ ውሳኔ ነው። አንድ ሰው ቃል ኪዳን ከገባ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር የገባውን ቃል ኪዳን ማክበር ይጠበቅበታል። ተማሪዎች ይህን እውነታ እንዲያውቁ ከተደረገ በኋላ እነሱ በቤት ውስጥ ሊያዳብሯቸው የሚገቡ ቃል ኪዳኖች ምን እንደሆኑ እንዲወያዩባቸውና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱባቸው ማድረግ። |
| • ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት የመወጣት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣ | 6.2 ቅንነት፣ ታማኝነትና ሐቀኝነት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት የመወጣት አስፈላጊነት፣ | • ገበሬ አምርቶ እህሉን ወደ ገበያ የማውጣት ኃላፊነት አለበት። የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ሰዓቱን አክብሮ ሥራውን የመሥራት ኃላፊነት አለበት። የመኪና ሾፌር ፍጥነቱን ጠብቆና የቀኝ መንገዱን ይዞ መንዳት ይጠበቅበታል። እያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ካልተወጣ በስተቀር ሰላማዊ ኑሮ መኖር አይቻልም። አንድ ሰው ኃላፊነቱንም ሲወጣ ተወጣ እንዲባል ብቻ ሳይሆን ውጤት በሚያመጣ መልኩ መሆን አለበት፣ ይህም እንዲሆን ሁሉም ኃላፊነቱን ለመወጣት ሥራዎቹን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት ማከናወን አለበት። በዚህ ረገድ ተማሪዎቹ በቤት፣ በትምህርት ቤት ወዘተ ኃላፊነታቸውን እንዴት መወጣት እንደሚገባቸው እንዲወያዩና በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና | 6.3 የተፈጥሮና ታሪካዊ | • ስለ ታሪካዊ ሀብትና ቅርስ በ5ኛ ክፍል ትምህርታቸው መጠነኛ ግንዛቤ አግኝተዋል። በዚህ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ቅርስን መንከባከብ ጠቀሜታዎች ይዘረዝራሉ፣<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን ከጥፋት ይጠብቃሉ፣ | ሀብትና ቅርስ፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>- የተፈጥሮ ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን ከጥፋት የመጠበቅ ኃላፊነት፣<br>-የተፈጥሮናታሪካዊ ሀብትና ቅርስን መንከባከብ ጠቀሜታ | የክፍል ደረጃ ደግሞ ያን ትምህርት መከለስና በአካባቢያቸው የሚገኙ ታሪካዊ ሀብቶችንና ቅርሶችን ለመጠበቅ በነሱ ደረጃ ምን ማድረግ እንደሚገባቸውና ታሪካዊ ሀብቶችና ቅርሶች መጠበቃቸውም የሚሰጡት ጠቀሜታ (በተለይም ከቱሪዝም ጋር በተገናኘ) ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይተው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |
| • የኤች አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ኤች አይ.ቪ/ኤድስ በታማሚውና በቤተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳይ ይዘረዝራሉ፣<br>• በደረጃቸው እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣<br>• በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተያዙ ሰዎች በአቅማቸው እንክብካቤ ያደርጋሉ፣ | 6.4 ኤች አይ.ቪ/ኤድስ፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>- የኤች አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች (ከ5ኛ ክፍል ትንሽ ሰፋ ባለ ነገር ግን የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ባላካተተ)፣<br>- በኤች አይ.ቪ/ኤድስ የታመመ ሰው የሚደርሱበት ችግሮች፣<br>- የኤች አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ በቤተሰብ ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት፣ | • ተማሪዎቹ በ5ኛ ክፍል ላይ የተማሩትን የኤች አይ.ቪ/ኤድስ ትምህርት እንዲያስታውሱት ማድረግ። በዋንኛነት በሽታው መድሃኒት ያልተገኘለት መሆኑን እንዲያስታውሱት ማድረግ።<br>• በዛው በ5ኛ ክፍል ትምህርት ላይ መተላለፊያ መንገዱንም እንዲሁ ተምረዋልና ያንን ማስታወሳቸውን ማወያየት። ሌሎች የበሽታው መተላለፊያ መንገዶችን ለምሳሌ ከበሽተኛው ሰው ወደ ጤነኛው ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ደም ከገባ በሽታው ሊተላለፍ እንደሚችል ማስረዳትና ማወያየት። ከተቻለ በቡድን ተከፋፍለው በአካባቢያቸው በበሽታው የተጠቁ ግለሰቦች በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ተመልክተው እንዲሁም እነሱ በደረጃቸው ለበሽታው ተጠቂዎች ሊያደርጉላቸው የሚገቡ እንክብካቤዎችን (ፍቅር ማሳየት፣ አለማግለል፣ ወዘተ) በተመለከተ በክፍል ውስጥ ትምህርት እንዲያቀርቡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በቤተሰብ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የቃል ኪዳን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት የመወጣት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን መንከባከብ ጠቀሜታዎች ይዘረዝራሉ፣በአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን ከጥፋት ይጠብቃሉ፣የኤች አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣ኤች አይ.ቪ/ኤድስ በታማሚውና በቤተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳይ ይዘረዝራሉ፣በደረጃቸው እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተያዙ ሰዎች በአቅማቸው እንክብካቤ ያደርጋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** በቤተሰብ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የቃል ኪዳን ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፣ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት የመወጣት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን መንከባከብ ጠቀሜታዎች ይዘረዝራሉ፣በአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን ከጥፋት ይጠብቃሉ፣የኤች አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣ኤች አይ.ቪ/ኤድስ በታማሚውና በቤተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳይ ይዘረዝራሉ፣በደረጃቸው እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ይጠብቃሉ፣በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተያዙ ሰዎች በአቅማቸው እንክብካቤ ያደርጋሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 7. ጠንካራ የሥራ ባህል

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- የሥራን ክቡርነት ይረዳሉ።
- ጠንክሮ የመሥራትና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋልን ጥቅም ይገነዘባሉ።
- በኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት ውስጥ የተደነገጉ ኢኮኖሚና የልማት ነክ ዓላማዎችን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ጠንክሮ መሥራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋል ጥቅምን ያብራራሉ፣<br>• ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መብላት ከምግባርና ከእድገት አንፃር የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣ | 7.1 ጠንካራ የሥራ ባህል ምንነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>7.1.1 ጠንክሮ መሥራት፣<br>7.1.2 ሥራን አለመናቅ፣<br>7.1.3 ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል፣<br>7.1.4 ሥራን አለመናቅና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ለራስና ለሀገር ያለው ጠቀሜታ፣ | • ተማሪዎቹን በሦስት ቡድን በመክፈል ጠንክሮ መሥራት፣ ሥራን አለመናቅና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል በሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው በየቡድን መሪያቸው አማካኝነት የተወያዩባቸውን ሀሳቦች ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ።<br>• በዚሁ ውይይት ላይ ጠንክሮ መሥራት፣ ሥራን አለመናቅና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ለራስም ሆነ ለሀገር የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲያስረዱና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ሳይሰሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገልፃሉ፣<br>• ሳይሰሩ መብላትን ይፀየፋሉ፣ | 7.2 ሳይሰሩ መብላት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>7.2.1 ሳይሰሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰው ጉዳት፣ | • ተማሪዎች ባለፈው ትምህርት ክፍለ ጊዜ ጠንክሮ መሥራትና ሥራን አለመናቅን በተመለከተ የጋራ መግባባት ፈጥረዋል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ደግሞ ሳይሰሩ መብላት ምን ማለት እንደሆነ በክለሳ መልክ እንዲወያዩበት ማድረግ፤ በማስከተልም በቡድን ተከፋፍለው ሳይሰሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት እንዲወያዩባቸውና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባርን | 7.3 የሙያ ችሎታና የሙያ | • የሙያ ችሎታ አንድ ሰው አንድን ነገር (ምን ለመሥራት፣ ግምብ ለመገንባት፣ መኪና |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይገልፃሉ፣<br>• የሙያ ሥነምግባር መጓደል በዜጐች ላይ የሚያደርሰውን ችግር ያብራራሉ፣ | ሥነምግባር ፣<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>7.3.1 የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባር ምንነት፣<br>7.3.2 የሙያ ሥነምግባር መጓደል በዜጐች ላይ የሚያደርሰው ችግር፣ | ለመጠገን ወዘተ) ለመሥራት ያለውን ብቃት የሚያመላክት ነው። የፈለገው የሙያ ችሎታ ቢኖረው አንድ ሰው ሙያው የሚፈለገው ሥነምግባር ከሌለው ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ካለመቻሉም በላይ በሙያው ተጠቃሚ የሆኑ ዜጐች ሊጐዱ ይችላሉ። ለተማሪዎቹ ይህን ጉዳይ በምሳሌ በማስረዳት (ለምሳሌ የህክምና አዋቂዎችን ጉዳይ) ነገሩ እንዲገባቸው ከተደረገ በኋላ በውይይት አዳብረውት የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት የልማት ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣ | 7.4 ጠንካራ የሥራ ባህልና ልማት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>7.4.1 የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት የልማት ዓላማዎች፣ | • ጠንክሮ ከተሰራ ልማትን ማረጋገጥ እንደሚቻል ተማሪዎች እንዲገነዘቡት ማድረግ። ጠንክሮ ለመሥራት ደግሞ ከራስ ተነሳሽነት፣ የሙያ ችሎታን ከማዳበርና የሙያ ሥነምግባርን ከመያዝ ባሻገር የዜጐች መብቶች ተከብረውና የልማት ዓላማዎችም ሕገመንግሥታዊ እውቅና አግኝተው መገኘት አለባቸው። በዚህ ረገድ የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት ለዜጐች መብቶች እውቅና ከመስጠቱም ባሻገር የልማት ዓላማዎችንም ይዟል። ተማሪዎች ይህን እንዲገነዘቡ የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት ስለልማት የሚያወሳውን እንዲያነቡትና እንዲወያዩበት ማድረግ።<br>• ሕገመንግሥቱ ልማትን ለማፋጠን የሚኖረውን ጠቀሜታም በውይይታቸው ወቅት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲወያዩበትና የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ፣ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ጠንክሮ መሥራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋል ጥቅምን ያብራራሉ፣ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መብላት ከምግባርና ከእድገት አንፃር የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣ሳይሰሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ሳይሰሩ መብላትን

6ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

ይፀየፋሉ፣የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባርን ይገልፃሉ፣የሙያ ሥነምግባር መጓደል በዜጐች ላይ የሚያደርሰውን ችግር ያብራራሉ፣የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት የልማት ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ጠንክሮ መሥራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋል ጥቅምን ያብራራሉ፣ሥራን መናቅና ሳይሰሩ መብላት ከምግባርና ከእድገት አንፃር የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይዘረዝራሉ፣ሳይሰሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰውን ጉዳት ይገልፃሉ፣ሳይሰሩ መብላትን ይፀየፋሉ፣የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነምግባርን ይገልፃሉ፣የሙያ ሥነምግባር መጓደል በዜጐች ላይ የሚያደርሰውን ችግር ያብራራሉ፣የኢ.ፌዴሪ ሕገመንግሥት የልማት ዓላማዎችን ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

8. ራስን መቻል

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣ የተመደበው ክፍለ ጊዜ 7

- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትን ምንነት ይገነዘባሉ።
- የራሳቸውን ፅኑ እምነት ከሌሎች ሰዎች ሃሳብ ጋር የማጣጣምን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ራስን መቻል ለምን እንደሚጠቅም ያብራራሉ፣ | 8.1 ራስን የመቻል ጠቀሜታ፣<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>- የእኩልነት ስሜትን ለመፍጠር፣<br>- የተመፅዋችነት ስሜትን ለማስወገድ፣<br>- በራስ የመተማመን ስሜትን ለመፍጠር፣<br>- በራስ የመተማመን ጠቀሜታዎች፣ | • በመጀመሪያ ራስን መቻል ማለት ምን ማለት እንደሆነና በነሱ ደረጃ እንዴት እንደሚገለጥ ተማሪዎቹ በየተራ እንዲያስረዱ ማድረግ። ቀጥሎም አንድ ጉዳይ (Case study) በማቅረብ ተማሪዎቹ ይህ ጉዳይ እንዴት የእኩልነትና በራስ የመተማመን ስሜትን እንደሚፈጥር፤ በሌላ በኩል እንዴት የተመፅዋችነት ስሜትን ለማስወገድ እንደሚረዳ እንዲወያዩባቸው ማድረግ። ለምሳሌ በፈተና ወቅት ለሚፈተኑት ትምህርት በደንብ ዝግጅት አድርገው፣ ዝግጅት በማድረጋቸውም ፈተናውን እንደሚሰሩት እርግጠኞች ሆነው ሲቀርቡ የሚሰማቸው ስሜት ምን ሊሆን እንደሚችል በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ። |
| • ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ምንነትን ይገልፃሉ፣ | 8.2 ጥገኝነት፡<br>(2 ክፍለ ጊዜ)<br>8.2.1 ጥገኝነት ምንድን ነው?<br>8.2.2 ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት፣<br>- የኮንትሮባንድ ንግድ፣ | • ይህን ትምህርት ጥገኝነትን በመግለጽ መጀመር። ጥገኝነት አንድን ጥቅም (ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ) በራስ ችሎታ፣ በራስ ጥረት፣ ወዘተ ለማግኘት ሳይሆን በሌሎች ላይ ተንጠልጥሎ ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው። ለምሳሌ ተማሪ በራሱ ጥረት አጥንቶ ፈተና በመሥራት ከማለፍ ይልቅ ኮርጆ ለማለፍ ሲጥር ይህ የጥገኝነት መገለጫ ነው። ልክ እንደዚሁ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን ለማግኘት በራሳቸው ጥረት ሳይሆን በሌሎች አማካኝነት ለማግኘት የሚፈልጉ ወገኖች አሉ። ለምሳሌ በዚህ ረገድ የኮንትሮባንድ ንግድ ተጠቃሽ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች እነዚህ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትን የሚያራምዱ ወገኖች እነማን እንደሆኑና መገለጫ ባህሪያቸው ምን እንደሆነ እንዲሁም ይህ መጥፎ ባህሪ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች አስመልክቶ እንዲወያዩ በማድረግ የራሳቸውን |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | - የኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣<br>- የኮንትሮባንድ ንግድ በማህበራዊ መረጋጋት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣ | ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በራስ መተማመን የሚገለጽባቸውን ባህሪያት ይዘረዝራሉ፣<br>• በራሳቸው የመተማመን ዝንባሌን ይላበሳሉ፣<br>• የሌሎችን ሰዎች አስተሳሰብ በአግባቡ ያስተናግዳሉ፣ | 8.3 በራስ መተማመን፣<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>8.3.1 በራስ የመተማመን ባህሪ የሚገለጽባቸው መንገዶች፣<br>- ስለራስ ትክክለኛ ግንዛቤ መያዝ፣<br>- የራስን አስተሳሰብ ከሌሎች አስተሳሰብ ጋር ማስማማት፣<br>- ስለራሳችን የሚኖረንን የተሳሳተ ግንዛቤ ማስተካከል፣<br>- ስህተትን አምኖ መቀበል፣<br>- የሌሎችን አስተሳሰብ ማስተናገድ፣ | • ተማሪዎች በራስ መተማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልፁ ማድረግ። አንድ ሰው በመጀመሪያ በራሱ የሚተማመን ካልሆነ በሥራውም ሆነ በኑሮው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ አንድ ተማሪ በራስ የመተማመን መንፈስ ፈተና ካልሠራ ጥሩ ውጤት ሊያመጣ አይችልም። ከሌሎች በመኮረጅ ጥሩ ውጤት ቢያመጣ እንኳን ይህ በጥገኝነት የመጣ ነውና ዘላቂነት አይኖረውም። በራሱ የሚተማመን ሰው ደግሞ ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ስለሚኖረው የራሱን አስተሳሰብ ከሌሎች ጋር ለማስማማትም ሆነ ስህተቶቹን ለማረም የሚቸገር አይሆንም። በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩና በነጥቦቹ ላይ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ራስን መቻል ለምን እንደሚጠቅም ያብራራሉ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ምንነትን ይገልፃሉ፣በራስ መተማመን የሚገለጽባቸውን ባህሪያት ይዘረዝራሉ፣በራሳቸው የመተማመን ዝንባሌን ይላበሳሉ፣የሌሎችን ሰዎች አስተሳሰብ በአግባቡ ያስተናግዳሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ራስን መቻል ለምን እንደሚጠቅም ያብራራሉ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ምንነትን ይገልፃሉ፣በራስ መተማመን የሚገለጽባቸውን ባህሪያት ይዘረዝራሉ፣በራሳቸው የመተማመን ዝንባሌን ይላበሳሉ፣የሌሎችን ሰዎች አስተሳሰብ በአግባቡ ያስተናግዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 9. የቁጠባ ባህል

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 7**

- ቁጠባ ያለውን ጠቀሜታ ያውቃሉ።
- አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ የቁጠባ አንዱ መገለጫ መሆኑን ይረዳሉ።
- ራስን በአቅም ልክና በእቅድ በመምራት እንዴት የቆጠባ ባህልን ማዳበር እንደሚቻል ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የቁጠባን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣<br>• ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• ንብረታቸውን በቁጠባና በእንክብካቤ ይይዛሉ፣<br>• ቤተሰቦቻቸው በቁጠባ እንዲኖሩ ይመክራሉ፣ | 9.1 ቁጠባ፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.1.1 የቁጠባ ጠቀሜታ፣<br>9.1.2 ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎች፣<br>- አላስፈላጊ ወጪዎችን ማስወገድ ወይም መቀነስ፣<br>- ራስንና ቤተሰብን በእቅድና በአቅም ማስተዳደር፣ | • በ5ኛ ክፍል ትምህርት የቁጠባን ምንነትና ዓላማዎች እንዲያውቁ ተደርጓል። እዚህ ጋ ደግሞ የቁጠባን ጠቀሜታ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል። ለዚህም እንዲረዳ ቁጠባ ጠቃሚ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• ጠቃሚነቱ ላይ መተማመን ላይ ከተደረሰ በኋላ ቁጠባን ተግባራዊ ለማድረግ እነሱ የመቆጠቢያ ዘዴዎች የሚሏቸውን እንዲገልፁና አላስፈላጊ ወጪዎችን ማስወገድ ወይም መቀነስ እንዲሁም ራስንና ቤተሰብን በእቅድና በአቅም በመምራት እንዴት ቁጠባን እንደሚያስፋፉ፤ እነሱም በአቅማቸው ቤተሰቦቻቸው በእቅድና በአቅማቸው ልክ እንዲኖሩ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ። |
| • በአካባቢያቸው የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣ | 9.2 በአካባቢ የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ተግባራት፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.2.1 የቁጠባ ባህልን የሚጐዱ አካባቢያዊ ልማዶች፣ | • በየቦታው የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ጐጂ ልማዶች እንዳሉ ይታወቃል። ስለሆነም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ቤተሰቦቻቸውን ወይም ማንኛውንም ሰው በመጠየቅ በአካባቢያቸው የቁጠባ ባህል እንዳይዳብር እንቅፋት የሚሆኑ አሰራሮች፣ ልማዶች ወይም ባህሎችን እንዲለዩና በክፍል ውስጥ ውይይት እንዲያካሂዱባቸው ማድረግ። |
| • የድህነትን አስከፊነት ይገልፃሉ፣<br>• ድህነትን ለመዋጋት ሊወሰዱ ስለሚገቡ እርምጃዎች ያብራራሉ፣ | 9.3 ድህነት፣<br>9.3.1 የድህነት አስከፊነት፣<br>(3 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.3.2 የአባካኝነትና የድህነት ዝምድና፣ | • በነሱ አረዳድ በአካባቢያቸውና በሀገር ደረጃም ድህነትን እንዴት እንደሚገነዘቡትና ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ እንዲገልጹ ማድረግ። ለምሳሌ ያህልም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ድህነት እህልና ልባሽ ጨርቆችን እስከ መመጽወት ይደርሳል። ተማሪዎቹ በዚህ መልኩ የድህነትን አስከፊነት መረዳታቸውን ማረጋገጥ። የድህነትን አስከፊነት ተማሪዎቹ ከተረዱ ይህን አስከፊ ድህነት ለማስወገድ በእነሱ ደረጃ፣ በአካባቢያቸው ደረጃና በሀገር ደረጃ ምን ሊደረጉ እንደሚገባቸው |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | 9.3.3 ድህነትን ለማጥፋት ወጪን መቀነስና ቁጠባን መልመድ፣ | እንዲወያዩና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ለምሳሌ በነሱ ደረጃ ልብሶቻቸውን፣ የትምህርትና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን በቁጠባና በጥንቃቄ ከተጠቀሙ አባካኝነትን ያስወግዳሉ፤ በዚህ የተነሳ አላስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይቀንሳሉ ማለት ነው። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፣ንብረታቸውን በቁጠባና በእንክብካቤ ይይዛሉ፣

- ቤተሰቦቻቸው በቁጠባ እንዲኖሩ ይመክራሉ፣በአካባቢያቸው የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣የድህነትን አስከፊነት ይገልፃሉ፣ ድህነትን ለመዋጋት ሊወሰዱ ስለሚገቡ እርምጃዎች ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባን አስፈላጊነት ይገልፃሉ፣ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ፣ንብረታቸውን በቁጠባና በእንክብካቤ ይይዛሉ፣

- ቤተሰቦቻቸው በቁጠባ እንዲኖሩ ይመክራሉ፣በአካባቢያቸው የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣የድህነትን አስከፊነት ይገልፃሉ፣ ድህነትን ለመዋጋት ሊወሰዱ ስለሚገቡ እርምጃዎች ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

10. **ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 6**

- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።
- ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ የሚጠይቁ አካባቢያዊ ጉዳዮችን ያውቃሉ።
- በአካባቢያቸው የሚገኙ የሲቪክ ማህበራትን ተግባራት ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በትምህርት ቤት በሚካሄዱ የሥራ ዘመቻዎችና ውሣኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• በተለያዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ውስጥ መሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ፣ | 10.1 የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት፣<br>(3 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- በትምህርት ቤት በሚካሄዱ የሥራ ዘመቻዎችና ውሣኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ፣<br>- በትምህርት ቤት ጉዳዮችላይ በጋራ መወሰን፣ | • እስከ አሁን በተማሯቸው ትምህርቶች የሕዝባዊ ተሳትፎን ምንነት እንደሚያውቁ ይገመታል። ስለዚህ ትምህርቱን እንዲከልሱ ከተደረገ በኋላ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የነሱን ተሳትፎ የሚፈልጉ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑና ለነዚህም ጉዳዮች የእነሱ ምላሽ ምን ምን መሆን እንዳለባቸው እንዲወያዩ ማድረግ።<br>• ውይይታቸው በተመለከቱት ይዘቶች ዙሪያ እንዲያጠነጥኑ ማድረግ ጠቃሚነት ይኖረዋል። በቡድን የተወያዩበትንም በክፍል ውይይት በማጠናከር የጋራ አቋም እንዲይዙ ማድረግ። |
| • የሲቪክ ማህበራትን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣<br>• በሲቪክ ማህበራት የመሳተፍ ጠቀሜታን ይገልጻሉ፣<br>• በትምህርት ቤታቸው ባሉት የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣ | 10.2 በሲቪክ ማህበራት ተደራጅቶ መሳተፍ ያለው ጠቀሜታ፣<br>(3 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- ዜጐችን በአንድ ዓላማ ዙሪያ በማሰባሰብ ለተግባራዊ እን ቅስቃሴ ማነሳሳት፣ | • የሲቪክ ማህበራት ምንነትን እንዲከልሱ ከተደረገ በኋላ በማህበራቱ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ያለውን ፋይዳ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ። ምን ጊዜም ሕብረት ኃይል ነው፣ ከነተረቱ « ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ » ይባላል።<br>• ተማሪዎች ይህን እንዲረዱና ውይይታቸውን በዚህ ዙሪያ እንዲያካሂዱ በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | - ዜጎች ለሕዝብ ጥቅም እንዲሠሩ ለማድረግ፣<br>-የሥራ ፍቅርን ለማዳበር፣ | |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በትምህርት ቤት በሚካሄዱ የሥራ ዘመቻዎችና ውሣኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣
በተለያዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ውስጥ መሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ፣የሲቪክ ማህበራትን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በሲቪክ ማህበራት የመሳተፍ ጠቀሜታን ይገልጻሉ፣
በትምህርት ቤታቸው ባሉት የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** በትምህርት ቤት በሚካሄዱ የሥራ ዘመቻዎችና ውሣኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣
በተለያዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ውስጥ መሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም ይገልፃሉ፣የሲቪክ ማህበራትን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣በሲቪክ ማህበራት የመሳተፍ ጠቀሜታን ይገልጻሉ፣
በትምህርት ቤታቸው ባሉት የሲቪክ ማህበራት ይሳተፋሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 11. ዕውቀትን መሻት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- የዕውቀትን ዋና ዋና ምንጮች ያውቃሉ።
- የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ባህሪያትን በመለየት የዕውቀትን ጠቀሜታ ይረዳሉ።
- የንባብ ልምድና የመረጃ አያያዝ ቅጥምን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የእውቀት ምንጮችን ይዘረዝራሉ፣ | 11.1 ዋና ዋና የእውቀት ምንጮች፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>- አካባቢ፣<br>- ሕብረተሰብ፣<br>- ትምህርት ቤት፣<br>- መምህራን፣<br>- መጽሐፍት፣<br>- ተማሪዎች፣ | • ተማሪዎች የራሳቸውን የዕውቀት ትርጉም እንዲሰጡ በማድረግ ትምህርቱን መጀመር። ብዙ ጊዜ የሚታሰበው ዕውቀት ከትምህርት ቤት ብቻ የሚገኝ ተደርጐ ነው። ዕውቀት ግን በተለያዩ መንገዶች እንደሚገኝ እሙን ነው።<br>• ስለዚህ ተማሪዎቹን በቡድን በመከፈልና በይዘትነት የተመለከቱትን ነጥቦች በማከፋፈል እንዴት እነዚህ ይዘቶች የዕውቀት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተወያይተው ለክፍላቸው ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ለዕውቀት መዳበር እንዴት እንቅፋት እንደሚሆኑ ይገልፃሉ፣<br>• የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት መገለጫዎችን ይተነትናሉ፣ | 11.2 ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>- የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ለዕውቀት መዳበር እንቅፋት መሆን፣<br>- የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ባህሪያት | • በአካባቢያቸው አሉ የሚሏቸውን ኋላቀር አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን ከቻሉ በራሳቸው ካልቻሉ ሰውም ጠይቀው ቢሆን እንዲያቀርቡ ማድረግ። ለምሳሌ ባዕድ አምልኮ ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ሲሆን የሰው ልጅ ተመራምሮና በራሱ ጥረት ዕውቀቱን በማዳበር ለውጥ እንዳያመጣ እንቅፋት የሚሆን ነው፤ ይህ ደግሞ እድገትን ይገታል።<br>• ለተማሪዎች በይዘትነት የተመለከቱትን ነጥቦች በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩባቸውና እንዴት ኋላቀር አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ለእድገት እንቅፋት እንደሆኑ በራሳቸው ድምዳሜላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | መገለጫዎች፣<br>- በራስ አለመተማመን፣<br>- በዕድል ብቻ ማመን፣<br>- ተስፋ መቁረጥ፣<br>- ባዕድ አምልኮ፣ | |
| • የመረጃ ዓይነቶችን ያስረዳሉ፣<br>• የትምህርት መረጃ አያያዝን ይገልፃሉ፣ | 11.3 መረጃ፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- የመረጃ ዓይነቶች፣<br>- የመረጃ አያያዝ፣<br>- የግል መረጃ አያያዝ፣<br>- የትምህርት መረጃ አያያዝ<br>- የአካባቢ መረጃ አያያዝ፣ | • ለማንኛውም ነገር መረጃ አስፈላጊ ነገር ነው። ያለ ትክክለኛ መረጃ ምንም ዓይነት ሥራ ማከናወን አይቻልም። መረጃን ማግኘት ብቻ ሳይሆን መረጃ በአግባቡ መያዝ አለበት። ለምሳሌ ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን ስለሆነ ጉዳይ አንድ መረጃ ቢሰሙ ያንን መረጃ በማስታወሻ ደብተር ላይ መረጃውን ከየት እንዳገኙት፣ መቼ እንዳገኙት ጽፈው ካላስቀመጡት በቃል የተያዘ መረጃ መረሳቱ የማይቀር ነው። ከመረሳቱም ባሻገር ይህ ምንጩ ያልታወቀን መረጃ አገልግሎት ላይ ለማዋል በጣም አዳጋች ጉዳይ ነው።<br>• ከመጽሐፍት የተገኘንም መረጃ በሚመለከት መረጃው የተገኘበት መጽሐፍ፣ የመጽሐፉ ደራሲ፣ አሳታሚው ድርጅት፣ መጽሐፉ የታተመበት ዓመተ ምህረት ተጠቅሶ መረጃው መያዝ አለበት። ዋናው ቁም ነገር መረጃ አገልግሎት ላይ መዋል በሚችል መልኩ መያዝ አለበት፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ተማሪዎቹ ከተወያዩ በኋላ የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ። |
| • ዘመናዊ የትምህርት አጠናን ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ | 11.4 የማንበብ ልምድ፣<br>(1 **ክፍለ ጊዜ**)<br>11.5 የትምህርት አጠናን ዘዴ፣1<br>( **ክፍለ ጊዜ**) | • ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የማንበብ ልምዳቸውን በከፍተኛ ደረጃ ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፣ የንባብ ባህላቸውን ከማዳበር ጐን ለጐን ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ መጽሐፍትን ለአጠቃላይ ዕውቀት ማንበብና ትምህርትን ማጥናት ልዩነት ያላቸው መሆኑን ነው፣ ትምህርታቸውን ለማጥናት ከሁሉ በፊት የጥናት ፕሮግራምሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን፤ ይህም ጥናታቸው ቅደም ተከተል እንዲኖረው ያደርጋል። በፕሮግራማቸው መሠረት ሲያጠኑም ሙሉ ትኩረታቸውን ጥናቱ ላይ አድርገው በማይረበሹበትና ፀጥታቸውን ሊያስተጓጉል የሚችል ነገር በሌለበት ሁኔታ መሆን አለበት። እንደ ትምህርቱ ባህሪም በጥናት ወቅት ጥናቱን በተግባር መለማመድ የሚያስፈልግ ከሆነ ያንን በማድረግ መሆን ይገባዋል። የአጠናን ዘዴን በተመለከተ ከተማሪዎቹ ጋር በክፍል ውስጥ የተግባር ልምምድ ማድረግና መልዕክቱን በደንብ እንዲጨብጡት ማስቻል። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የእውቀት ምንጮችን ይዘረዝራሉ፣ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ለዕውቀት መዳበር እንዴት እንቅፋት እንደሚሆኑ ይገልፃሉ፣ የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት መገለጫዎችን ይተነትናሉ፣የመረጃ ዓይነቶችን ያስረዳሉ፣ዘመናዊ የትምህርት አጠናን ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ፣የትምህርት መረጃ አያያዝን ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የእውቀት ምንጮችን ይዘረዝራሉ፣ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ለዕውቀት መዳበር እንዴት እንቅፋት እንደሚሆኑ ይገልፃሉ፣ የኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት መገለጫዎችን ይተነትናሉ፣የመረጃ ዓይነቶችን ያስረዳሉ፣ዘመናዊ የትምህርት አጠናን ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ፣የትምህርት መረጃ አያያዝን ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።